መልእክት አምስት

**የእግዚአብሔር ውጥን በኢዮብ—**
**መልካም ሰው አምላክ-ሰው መሆኑ**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ ኢዮብ 1፡1፣ 8፤ 2፡3፣ 9፤ 27፡5፤ 31፡6፤ 42፡ 5-6፤
ዮሐንስ 1፡14፤ ሮሜ 1፡3-4፤ 8፡29

**I. ኢዮብ ራሱን በፍጹምነቱ፣ በቅንነቱ እና በግብረገባዊነቱ የሚገልጥ መልካም ሰው ነበር— ኢዮብ 27፡5፤ 31፡6፤ 32፡1፦**

ሀ. ፍጹም መሆን ከውስጡ ሰው ጋር የተገናኘ ነው፣ ቅን መሆን ከውጪው ሰው ጋር የተገናኘ ነው—1፡1።

ለ. ኢዮብ ግብረገባዊነት ያለው ሰው ነበር፤ ግብረገባዊነት ፍጹም እና ቅን የመሆን ጥቅል-ድምር ነው—2፡3፣ 9፤ 27፡5፤ 31፡6፦

1. ከኢዮብ አንፃር፣ ግብረገባዊነት እርሱ የሆነው ነገር ሙሉ መገለጥ ነበር።
2. በባሕሪው ኢዮብ ፍጹም እና ቅን ነበር፤ ደግሞም በሥነ-ምግባሩ ከፍ ያለ ግብረገባዊነት ደረጃ ነበረው።

ሐ. ኢዮብ አዎንታዊ በሆነ መልኩ እግዚአብሔርን ፈራ፣ አሉታዊ በሆነ መልኩ ከክፋት ዞረ—1፡1፦

1. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው እንዲያው እንዲፈራው እና ምንም ስህተት እንዳይሠራ ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም ይገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ እንደምሳሌው ፈጠረ—ዘፍ. 1፡26።
2. እግዚአብሔርን መግለጥ እግዚአብሔርን ከመፍራት እና ከክፋት ከመዞር ከፍ ያለ ነው።
3. ኢዮብ በፍጹምነቱ፤ በቅንነቱ እና በግብረገባዊነቱ ያገኘው ነገር ሁሉ ከንቱ ነበር፤ የእግዚአብሔርን ኃሳብ አልፈጸመም ፍላጎቱንም አላረካም፣ ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ኢዮብ በፍቅር ግድ-ተሰኘ—ኢዮብ 1፡6-8፤ 2፡ 1-3

መ. እግዚአብሔር ብቻ ኢዮብ የሚያስፈልገው ነገር እንዳለ ያውቅ ነበር—በውስጡ እግዚአብሔር አልነበረውም፤ ስለዚህ ለአላማው መፈፀም ይገልጠው ዘንድ እግዚአብሔር ኢዮብ እርሱን እንዲያተርፈው ፈለገ—42፤5-6።

**II. የእግዚአብሔር ውጥን ኢዮብ እግዚአብሔርን በባህሪው የሚገልጥ አምላክ-ሰው እንዲሆን ነበር—22፡24-25፤ 38፡1-3፦**

ሀ. እግዚአብሔር ኢዮብን ወደሌላ ክልል፣ ወደ እግዚአብሔር ክልል አስገባው ይኸውም ኢዮብ በፍጹምነቱ፤ በጽድቁ እና በግብረገባዊነቱ ፈንታ እግዚአብሔርን ያተርፍ ዘንድ ነው—42፡5-6።

ለ. የእግዚአብሔር ውጥን ለእግዚአብሔር በክርስቶስ መገለጥ የእግዚአብሔር ሙላት ይሆን ዘንድ ኢዮብን የእግዚአብሔር አካል መልበስ በሆነው በክርስቶስ የተሞላ የእግዚአብሔር ሰው ማድረግ ነበር—1 ጢሞ. 6፡11፤ 2 ጢሞ. 3፡17።

ሐ. የእግዚአብሔር መግፈፍ እና መጨረስ እርሱን ለመስበር በኢዮብ ላይ ተንቀሳቅሰው ነበር ይኸውም እግዚአብሔርን ለመግለጥ ኢዮብ አምላክ-ሰው፣ ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወቱ እና በባሕሪው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አይነት መሆን ይችል ዘንድ [ኢዮብን] በእግዚአብሔር በራሱ እንደገና ለመገንባት እግዚአብሔር መሠረት እና መንገድ ያገኝ ዘንድ ነው—ኤፌ. 3፡16-21።

መ. እግዚአብሔር እኛን፣ በክርስቶስ ያሉ አማኞችን፣ መልካም ሰው እንድንሆን አይፈልግም፤ አምላክ-ሰው እንድንሆን ይፈልጋል—ዮሐ. 1፡12-13፤ ሮሜ 8፡16፦

1. እግዚአብሔር የፈጠረን በመልኩ እግዚአብሔርን ለመግለጥ ለሆነ አላማ ከመግዛቱ ጋር እርሱን ለመወከል ነው—ዘፍ 1፡26-28።
2. መልካም ሰው ብቻ ከሆንን፣ እግዚአብሔርን መግለጥ ወይም መወከል አንችልም።
3. እግዚአብሔርን የሚገልጥ እና እግዚአብሔርን የሚወክል ሰው መልካም ሰው ሳይሆን አምላክ-ሰው ነው—2 ቆሮ. 3፡18።
4. እግዚአብሔርን የሚገልጡ አምላክ-ሰዎች የእግዚአብሔር ወኪሎች የሆኑ እና በሁሉም ነገሮች ላይ የእግዚአብሔር ስልጣን ያላቸው ናቸው—ዘፍ 1፡27-28።

**III. የሦስታንዱ አምላክ አካል መልበስ እና መገለጥ የሆነው የክርስቶስ ተሠግዎ አምላክ-ሰውን አፈራ—ሉቃ 1፡31-32፤ ዮሐ. 1፡1፣ 14፣ 18፣ 51፦**

ሀ. የሉቃስ ወንጌል እንደ ይዘቱ በመለኮታዊው ሕይወት የተሞላ የሰብዕና ኑሮ የኖረው አምላክ-ሰው መገለጥ ነው—1፡35፤ 2፡7-16፣ 34-35፣ 40፣ 49፣ 52።

ለ. በክርስቶስ እግዚአብሔር እና ሰው አንድ አካል፣ አምላክ-ሰው ሆነዋል—1፡35፤ ዮሐ. 1፡14፤ ማቴ. 1፡18፣ 20-23፦

1. ጌታ ኢየሱስ ከመለኮታዊው ንጥረ-ነገር ስለተፀነሰ እና ከሰብዕና ንጥረ-ነገር ስለተወለደ፤ አምላክ-ሰው ሆኖ ተወልዷል፤ በመሆኑም፣ እንደ አምላክ ሰው ለመሆኑ ሁለት ውስጠ-ነገሮች ነበሩት—መለኮታዊ ውስጠ-ነገር እና የሰብዕና ውስጠ-ነገር—ቁ. 18።
2. ድንግል በሆነች ሰው ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መፀነስ፣ ሙሉ አምላክ እና ፍጹም ሰው የሆነውን አምላክ-ሰው በማፍራት የመለኮታዊ ባሕሪ ከሰብዕና ባሕሪ ጋር መዋሐድን አቀናበረ—ሉቃ. 1፡35።
3. እንደ ፍጹም ሰው እና እንደ ሙሉ አምላክ እግዚአብሔርን ለመያዝ እና በመለኮታዊ ባሕሪያት እርሱን ለመግለጥ ይህ አምላክ-ሰው የሰብዕና ባሕሪ ከሰናይ ባህሪያቱ ጋር አለው።

ሐ. እንደ አምላክ-ሰው ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በሰብዕና ሕይወቱ ሳይሆን በመለኮታዊው ሕይወት ኖረ—ዮሐ. 5፡18-19፣ 30፤ 6፡57፡-

1. ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ፤ ምንም እንኳን ሰው የነበረ ቢሆንም፤ በእግዚአብሔር ኖረ—ቁ. 57፤ 5፡19፣ 30፤ 6፡38፤ 8፡28፤ 7፡16-18፡-
   ሀ. ጌታ ኢየሱስ በሁሉም ነገር እግዚአብሔርን ኖረ እግዚአብሔርንም ገለጠ፤ እርሱ ያደረገው ነገር ሁሉ በእርሱ ውስጥ እና በእርሱ በኩል የእግዚአብሔር ማድረግ [ሥራ] ነበር—14፡10።
   ለ. ጌታ ኢየሱስ በሰብዕና ሕይወት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሕይወት እንደ አምላክ-ሰው ኖረ—6፡57።
   ሐ. የሰብዕና ኑሮው በሰብዕና ሕይወት ሳይሆን በመለኮታዊ ሕይወት ተኖረ—1፡4፤ 11፡25፤ 14፡6።
2. ጌታ ኢየሱስ ሁል ጊዜ የሰብዕና ሕይወቱን በመካድ—ሁል ጊዜ ራሱን በመስቀሉ ሥር በማድረግ—ስለኖረ፣ የሰብዕና ኑሮው ሰብዕናን ሳይሆን መለኮታዊ ባሕሪያት የሰብዕና ሰናይ ባሕሪያት በመሆናቸው መለኮትን ገለጠ—ማቴ. 16፡21፣ 24።
3. በምድር ላይ በኖራቸው ቀናት ራሱን ካደ መስቀሉንም ተሸከመ ይኸውም [የእግዚአብሔር] መለኮታዊ ባሕሪያት የሰብዕና ሰናይ ባሕሪያት በመሆናቸው እግዚአብሔርን ለመግለጥ እግዚአብሔርን መኖር ይችል ዘንድ ነው፤ ይህ እንደ ዋና ሞዴል የመጀመሪያው አምላክ-ሰው ኑሮ ነበር—ሉቃ. 1፡31-32፤ 7፡11-16፤ 10፡25-37፤ 13፡10-16፤ ሮሜ 8፡3፣ 29።

## IV. በመጀመሪያ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምላክ-ሰዉ ይናገራል፣ በትንሣኤው በኩል ይህ አምላክ-ሰው እንደ ብዙ አምላክ-ሰዎች ተራባ—ሮሜ 1፡3-4፤ 8፡29፤ ዕብ 2፡10፡-

ሀ. ጌታ ኢየሱስ፣ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው፣ ብዙ አምላክ-ሰዎችን፣ ርቢዎቹን ለማፍራት ዋናው ሞዴል ነው—1 ጴጥ. 2፡21።

ለ. እግዚአብሔር ሰው የሆነው የራሱን ብዙ ርቢ ለማግኘት በዚህም አዲስ ወገን ለማፍራት ነው፤ ይህ አዲስ ወገን የአምላክ-ሰው ወገን ነው—ሮሜ 8፡3፣ 29፤ ዕብ. 2፡10።

ሐ. አምላክ-ሰው የሆነው ጌታ ኢየሱስ እንደ ርቢዎቹ ብዙ ስንዴዎችን ለማፍራት ወደ ምድር የወደቀ የስንዴ ቅንጣት ነበር—ዮሐ. 12፡24፡-

1. የመጀመሪያው የስንዴ ቅንጣት—የመጀመሪያው አምላክ ሰው—ዋናው ሞዴል ነበር፣ በሞት እና በትንሣኤ በኩል በዚህ አንድ የስንዴ ቅንጣት የፈሩት ብዙ ስንዴዎች—ብዙ አምላክ-ሰዎች—የመጀመሪያው አምላክ-ሰው ርቢዎች ናቸው።
2. ብዙዎቹ ስንዴዎች እንደ ብዙ አምላክ-ሰዎች የእግዚአብሔር ርቢዎች ናቸው፤ እንዲህ አይነቱ ርቢ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል ምክንያቱም ርቢው እርሱን ይመስላል፣ እንደ እርሱ ይናገራል፣ እንደ እርሱ ይኖራል—1 ዮሐ. 2፡6፤ 3፡2፤ 4፡17።

መ. በአምላክ ሰው ርቢ የመጀመሪያው ደረጃ በመለኮታዊ ሕይወቱ እና ባህሪው ከእስትንፋሳዊው ክርስቶስ በመንፈሳችን ዳግም መወለድ አለብን—ዮሐ. 3፡3፣ 6።

ሠ. ለአምላክ-ሰዉ መራባት በነፍሳችን በእስትንፋሳዊው ክርስቶስ መለወጥ አለብን ይኸውም እርሱ በሰብዕናችን ለመገለጡ በእርሱ መለኮታዊ ባህሪያት የሰብዕና ሰናይ ባህሪያችን ከፍ እንዲደረግ፣ እንዲጠነክር፣ እንዲበለጥግ እና እንዲሞላ ነው—2 ቆሮ. 3፡17-18፤ ሮሜ 12፡2።

ረ. አምላክ-ሰዎች፣ ከእግዚአብሔር የተወለድን፤ የእግዚአብሔር ሕይወት እና ባህሪ ያለን እና የእግዚአብሔር ዝርያ እንደሆንን ማየት ያስፈልገናል—ዮሐ. 1፡12-13፡-

1. በመለኮታዊው ሕይወት ከእግዚአብሔር እንደተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች አምላክ-ሰዎች፣ መለኮታዊ ሰዎች ነን፤ ከተወለድንበት [ማንነት] ጋር አንድ አይነት ነን—1 ዮሐ. 3፡1፤ 5፡1።

2. ከእግዚአብሔር ስለተወለድን፣ በሕይወት እና በባህሪ ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሔር ነን ማለት እንችላለን—ዮሐንስ 1፡12-13፤ ሮሜ 8፡16፤ 2 ጴጥ. 1፡4።
3. ራሳችንን አምላክ-ሰው አድርጎ ማሰብ እና ማን እንደሆንን ማወቅ እና መገንዘብ በየእለቱ ባለን ልምምዳችን ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ይቀይረናል—1 ዮሐ. 2፡20፤ 3፡1-2፤ 5፡13፣ 20።
4. እኛ ክርስቲያኖች ወይም በክርስቶስ ያሉ አማኞች ብቻ አይደለንም፤ እኛ አምላክ-ሰዎች፣ የአምላክ-ሰው ወገን፣ የእግዚአብሔር ርቢዎች ነን—ዮሐ. 12፡24፤ ሮሜ 8፡16፣ 29፤ ዕብ. 2፡10-11።

## V. የክርስቶስ የአምላክ-ሰው ኑሮ ዋና ሞዴል አድርጎ አቀናበረው ይኸውም አምላክ-ሰዎች በሆንነው በእኛ ውስጥ መራባት እና ዳግም በእኛ መኖር ይችል ዘንድ ነው—ዮሐ. 14፡19፤ ገላ 2፡20፦

ሀ. እንደ አምላክ-ሰዉ ርቢ የአምላክ-ሰው ኑሮ መኖር ያስፈልገናል—ፊልጵ. 1፡19-21፤ 3፡10።

ለ. የክርስቶስ የስብዕና ኑሮ የእግዚአብሔርን ባህሪያት በስብዕና ሰናይ ባህሪያት ውስጥ ለመግለጥ ሰው እግዚአብሔርን መኖሩ ነበር፤ የስብዕና ሰናይ ባህሪያቱ በመለኮታዊ ባህሪያት ተሞልተው፣ ተዋሕደው እና ተጥለቅልቀው ነበር—ሉቃ. 1፡26-35፤ 7፡11-17፤ 10፡25-37፤ 19፡1-10።

ሐ. እንደ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው መስፋፋት፣ መጨመር፣ መራባት እና መቀጠል፣ እርሱ የኖረውን አይነት ኑሮ መኖር አለብን—1 ዮሐ. 2፡6፦

1. የጌታ የአምላክ-ሰው ኑሮ ለእኛ የአምላክ-ሰው ኑሮ ሞዴል አስቀምጦልናል—እግዚአብሔር በስብዕና ይገለጥ ዘንድ ለመኖር መሰቀል—ገላ. 2፡20።
2. ራሳችንን መካድ፣ የክርስቶስን ሞት መምሰል እና በተትረፈረፈው መንፈሱ እርሱን ማጉላት አለብን—ማቴ. 16፡24፤ ፊልጵ. 3፡10፤ 1፡19-21።
3. ራስ-ማዳበርን መቃወም እና የፍጥረታዊውን ሰው መገንባት መኮነን አለብን፤ የክርስቲያን ሰናይ ባህሪያት ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ ከመለኮታዊው ሕይወት፤ ከመለኮታዊው ባህሪ እና ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልገናል—ገላ. 5፡22-23።
4. የአምላክ-ሰውን ኑሮ የኖረው እርሱ ዛሬ በእኛ ውስጥ እና በእኛ በኩል የሚኖረው መንፈስ ነው፤ ከእርሱ ውጪ የትኛውም ነገር እንዲሞላን እና እንዲቆጣጠረን መፍቀድ የለብንም—2 ቆሮ. 3፡17፤ 13፡5፤ ኤፌ. 3፡16-19።

መ. በፊልጵስዩስ 1፡21 ያለው ክርስቶስ በፊልጵስዩስ 2፡5-8 ያለው አምላክ-ሰው ነው፤ ስለዚህ፣ ክርስቶስን መኖር በተትረፈረፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት በኩል አምላክ-ሰው የሆነውን [እርሱን] መኖር ነው—1፡19።

ሠ. ራሳችንን ለጌታ ስንከፍት፤ ስናፈቅረው እና ከእርሱ ጋር እንደ አንድ ለመጋጠም ስንሻ፣ በእርሱ እንሞላለን እንወረሳለንም፣ የመለኮትን ክብር እና የስብዕናን ሰናይ ባሕሪያት እንኖራለን—1 ቆሮ. 2፡9፤ 6፡17፤ ፊልጵ. 4፡4-9።

*© 2020 Living Stream Ministry*